# መመሪያ ቁጥር 9/2003 ዓ.ም

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግብር/አገልግሎት ክፍያ ይግባኝ ሰሚ ጉባዔዎችን ለማቋቋምና የአሰራር ስርዓታቸውን እና የአበል ክፍያ ለመወሰን የወጣ የማሻሻያ መመሪያ

በግብር አወሳሰን ቅር የተሰኘ ማንኛውም ግብር ከፋይ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ (2) እና በከተሞች ፋይናንስ ደንብ ቁጥር37/1998 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ካሟላ ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ በመሆኑ፣

እንዲሁም የጉባኤው አባላት በጉባኤው ላይ እየተገኙ ለሰሩበት ጊዜ አበል ሊከፈላቸው እንደሚገባ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 አንቀጽ 115 ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ የተደነገገ በመሆኑ እና ቀደም ብሎ የነበረው መመሪያ ከአዲሱ የሥራ ሂደት አኳያ ማለትም የክልልና የከተማ አገልግሎት ገቢዎች በአንድ የገቢ ሰብሳቢ ተቋም እንዲደራጁ የተደረገ ሲሆን ከዚህ በፊት የነበረው መመሪያ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል አግባብ ተቃኝቶ የተዘጋጀ ባለመሆኑ ይህን መመሪያ አሻሽሎ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 17(2) ይህን መመሪያ አውጥቷል።

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤዎች ማቋቋሚያ፣ የአሰራር ስርዓታቸውንና የአበል ክፍያ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር ገባ-9/2003 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

ሀ/ "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም ነው::

ለ/ "ከተማ" ማለት በአብክመ የከተሞችን አደረጃጀት ፈርጅ ለመወሰንና ለማቋቋም በወጣው ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 17/1996 ዓ.ም መሠረት ክልሉ ከተማ ብሎ የሚሰይመው አካባቢ ነው።

ሐ/ "ከተማ አስተዳድር" ማለት በህግ በታወቀ ወሰን ተደራጅቶ የአንድን ከተማ ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ፣የአስተዳድር፣ የልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥልጣንና ኃላፊነት በመረከብ የሚመራ የአካባቢ አስተዳድር ነው።

## *3. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን*

ይህ መመሪያ በክልሉ በሁሉም ደረጃ በሚገኙ ከተሞች ተለይቶ በተሰጣቸው የገቢ አርዕስቶች እንዲሁም በገቢዎች ባለስልጣን የገቢ መሠረቶች ላይ በመረጃ ላይ ተመስርተው በሚጥሉት ታክስ የአገልግሎት ክፍያ ላይ በሚቀርብ ቅሬታ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

4. ስለ ግብር ይግባኝ ጉባዔዎች መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የከተማ ፣የወረዳ አስተዳደሮች አምስት አባላት ያሏቸው እና ተጠሪነታቸው ለየሚመለከታቸው የከተማና የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤቶች የሆነ የግብር ይግባኝ ጉባዔ ይኖራቸዋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የሚቋቋመው ጉባዔ በወረዳው ስር ለሚገኙ የመሪና ንዑስ እንዲሁም ታዳጊ ከተሞች በደንብ ቁጥር69/2001 ዓ.ም መሰረት ተለይቶ በተሰጣቸው የገቢ አርዕስቶች ላይ በተለይም በመረጃ ላይ ተመስርቶ ግብር በመወሰን ገቢ ሲሰበስቡ የሚነሱ ቅሬታዎችን የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡፡
3. በባህር ዳር፣ በጎንደር፣ በደሴ፣ ከተሞች ለዚሁ ከተማ አስተዳደር ም/ቤት ተጠሪ የሆኑ ሁለት የግብር ይግባኝ ጉባኤዎች በተመሳሳይ ተቋቁመዋል፡፡
4. የጉባዔው የስራ ዘመን ለሁለት ተከታታይ አመታት እንዲያገለግሉ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር76/94 አንቀጽ115(6) መሠረት ተቋቁመዋል፡፡
5. ጉባዔዎቹ የየራሳቸው ጽ/ቤቶች ይኖሯቸዋል፡፡ ሆኖም ይህ ባልተቻለበት ሁኔታ በየደረጃው የሚሾሙትን የጉባዔ ሰብሳቢዎች ጽ/ቤቶች በተደራቢ በጽ/ቤትነት ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡

5. የጉባዔ አባላት አሰያየምና ስብጥር

1. የጉባዔ አባላት በግብር አወሳሰን ሂደት ቀጥተኛ ተሳትፎ ከሌላቸው፣ የግብር ማሻሻያ ኘሮግራሙን በማስፈፀም ሂደት ንግድ፣ ኢንዱስትሪንና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ለማስፋፋት ከሚሰሩና በየደረጃው ካሉ ሦስት የመንግሥት መ/ቤቶች የሚወከሉ ሶስት አባላትና በነጋዴው ህብረተሰብ የሚመረጡ ሁለት የነጋዴ ወኪሎች ይሆናሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የጉባዔ አባላት ስብጥር የሚከተለው ነው፡፡

ሀ/ በከተማ/ወረዳ አስተዳደሩ ከሚገኙ

1. የወረዳ/የከተማ አስተዳደር አቅም ግንባታ ጽ/ቤት የሚወክለው አንድ አባል
2. የወረዳ/የከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት የሚወክለው አንድ አባል
3. የወረዳ/የከተማ አስተዳደር ን/ኢ/ከ/ል/ጽ/ቤት የሚወክለው አንድ አባል

4. ከነጋዴው ህብረተሰብ ከሚወከሉ ሁለት አባላት ውስጥ አንዷ ሴት ብትሆን ይመረጣል፡፡

5. የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ገቢ ጽ/ቤት የሚወክለው አንድ አባል ድምጽ አልባ ፀሐፊ ይሆናል፤

ለ/ በዚሁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ከተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች የጉባኤ አባላት የሚመረጡበትን መመዘኛ ሙሉ መስፈርቶች የሚያሟ ላ ካ ል ተ ገ ኘ ከሌሎች መስሪያ ቤቶች መምረጥ ይቻላል፣

ሐ/ ሁለት ጉባዔ እንዲቋቋምባቸው በተወሰነላቸው ገቢ ጽ/ቤቶች በዚሁ አንቀጽ 2 ሀ እና ለ መሠረት ሆኖ ቁጥራቸውን በመጨመር ይከናወናል፣

3. ከመንግሥት መ/ቤቶች የሚወከሉ የጉባዔ አባላት አግባብነት ባለው መ/ቤት አቅራቢነት በአስተዳዳሪው ወይም በከንቲባው ይሾማሉ፤ ሹመታቸውም በከተማው/በወረዳ አስተዳደር ምክር ቤቱ ይፀድቃል፡፡

4. ከነጋዴው ህብረተሰብ የሚወከሉ የጉባዔ አባላት በከተማው የንግድ ምክር ቤት አቅራቢነት በአስተዳደር ምክር ቤቱ ይሰየማሉ፡፡ ሆኖም ጉባዔው በሚቋቋምበት ከተማ የንግድ ምክር ቤት ጽ/ቤት ከሌለ በወረዳ አስተዳደሩ አስተባባሪነት በነጋዴው ህብረተሰብ ተመርጠው በአስተዳደር ምክር ቤቱ ይሰየማሉ፡፡

5. የየጉባዔዎቹ ሰብሳቢዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ  አንቀጽ 2 ከተዘረዘሩት መካከል አግባብ ባለው የአስተዳደር  ምክር ቤት ተመርጠው ይሾማሉ፡፡

6. የጉባዔ አባላት የሚመረጡበት መመዘኛ

በሚቋቋሙት የይግባኝ ሰሚ ጉባዔዎች የጉባዔ አባላት የሚመረጡባቸው መመዘኛዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

ሀ/ ከመንግሥት መ/ቤቶች የሚወከሉ አባላት

1. በመልካም ሥነ ምግባር የታወቁና የሥነ ምግባር ችግር የሌለባቸው፣

2. ጉዳዮችን ከፍትሃዊነት አንፃር ገምግመው ውሳኔ ለመስጠት ፈቃደኝነቱና ችሎታው ያላቸው፣

3. ስለከተማው የንግድ እንቅስቃሴ የተሻለ ዕውቀት  ያላቸው፣

4. በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ላይ የተሻለ ግንዛቤ ያላቸውና መንግስት መልካም አስተደደርን ለማስፈንና ልማትን ለማምጣት በሚያደርገው ጥረት የጐላ ተሳትፎ ያላቸው፣

ለ/ የነጋዴ ተወካዮች

1. በንግድ ሥራ የካበተ ልምድ ያላቸውና ተፈላጊውን የግብር ግዴታ በመወጣት ረገድ መልካም አርአያ መሆን የሚችሉ፣
2. በአካባቢው ሕብረተሰብ ዘንድ በጥሩ ሥነ ምግባር የሚታወቁ፣
3. ቢቻል የንግድ ምክር ቤት አባላት የሆኑ፣

ለጉባዔው አባልነት የተመረጡ ተወካዮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አባላትን መርጦ የሚያቀርበው አካል ይሆናል፣

ጉባዔው ወይም የጉባዔው አባላት ከግብር ጋር በተያያዘ ማናቸውም ዓይነት የዲስፕሊን ችግር እንዳለባቸው ሲረጋገጥ በአቋቋማቸው አካል ከጉባዔ አባልነታቸው እንዲነሱ ተደርጐ በህግ እንዲጠየቁ ይደረጋል፣

7. የጉባዔ አባላት ግዴታዎች

1. የጉባዔው አባላት የጉባዔውን የአሰራሩ ምስጢር የመጠበቅ ኃላፊነትና ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሠረት የተሰየሙ የጉባዔ አባላት የቀረበላቸው ጉዳይ ከግል ጥቅማቸው፣ በጋብቻ ወይም በሥጋ ዝምድና ከሚተሳሰሩአቸው ወይም በፀብ ከሚገናኙአቸው ሰዎች ጋር የተያያዘ መሆኑን የተረዱ እንደሆነ ከውሳኔ በፊት ለሰብሳቢው አሳውቀው ይኸው ጉዳይ እልባት እስኪያገኝ ድረስ ከጉባዔው መነሳት ይኖርባቸዋል፡፡

8. ምልዐተ ጉባዔ

በእያንዳንዱ የስብሰባ ጊዜ የጉባኤው ሰብሳቢ በሚያወጣው ፕሮግራም መሰረት ከጉባዔው አባላት መካከል ሶስቱ ሲገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከሶስቱ አንዱ የነጋዴ ተወካዬች መሆን አለበት፡፡

9. የጉባዔው የስብሰባ ጊዜ፣የአሠራርና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

1. ጉባዔው ሥራውን የሚያከናውነው በገቢ ግብር አዋጅና በከተሞች ፋይናንስ ደንብ እንዲሁም በማስፈፀሚያ መመሪያዎች ላይ ተመስርቶ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉን በዝርዝር መከተል ሳያስፈልገው በተፋጠነ የክርክር አግባብ ይሆናል፡፡
2. በየደረጃው የሚገኙ ጉባዔዎች ቋሚ የመሰብሰቢያ ጊዜያቸውን አግባብ ላለው የአስተዳድር ምክር ቤት አቅርበው ያስወስናሉ፡፡

3. የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔው ይግባኝ ባይ ያቀረበው አቤቱታ ከገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ተገልብጦ እንደደረሰው ጉዳዩን አጣርቶ ውሳኔ ለመስጠት ከ10 የሥራ ቀናት በላይ መውሰድ የለበትም፡፡

4. ሰብሰቢው ቢያንስ 10 የሥራ ቀናት በላይ በሥራ ቦታው መገኘት የማይችል ከሆነ የሾመውን አካል አስታውቆ ከአባላቱ መካከል የተሻለውን መርጦ በሰብሳቢነት ሲሰራ እንዲቆይ ሊያደርግ ይገባል፡፡

5. ሁለት ጉባዔ በተሰየመባቸው ከተማ አስተዳደሮች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ጉዳዩ የቀረበለት ጉባዔ ስለግብር ከፋዩ በቂ መረጃ ከሌለውና ሁለተኛው ጉባዔ ስለግብር ከፋዩ የተሻለ ግንዛቤ ባለው በዚሁ ጉባዔ እንዲታይ ለማድረግ ተነጋግረው መስማማት ይችላሉ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሁለቱ ይግባኝ ሰሚ ጉባዔዎች ቀበሌዎችን ሊከፋፈሏቸው ይችላሉ፡፡

6. በዚሁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 5 ጉዳዩ ስምምነት ከተደረሰበት በግብር ከፋዩ የቀረበውን ማስረጃ በማስተላለፍ ሁኔታው ለግብር ከፋዩ ይገለፅለታል፡፡

7. ሁለት የግብር ይግባኝ ጉባኤ ባለባቸው ከተማ አስተዳደሮች ለገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ቅሬታ ሳያቀርቡ በቀጥታ ለይግባኝ ጉባኤ አቤቱታ በሚያቀርቡበት ወቅት አንደኛው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማመልከቻውን የተቀበሉበት ቀን በዚሁ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 5 ምክንያት ወደ ሁለተኛው የይግባኝ ጉባኤ ቢልከው የመጀመሪያው ይግባኝ ጉባዔ የተቀበለበት ቀን ይመዘገባል፡፡

8. የግብር ይግባኝ ጉባዔው በአገር ወይም በክልል እንዲሆም በከተማ ደረጃ ወጥነት ባለው መልኩ የሚሰራባቸው እንደ ትርፍ መቶ መተመኛና፣ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 11/14 እና19 ያሉትን የግብር ማስከፈያ ምጣኔ ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን እና የንግድና የአገልግሎት ግብርን ለመወሰን የተዘጋጀውን የነጋዴዎች ደረጃ መለያ መስፈርት ያሉትን ሊያስተካክል አይገባውም፡፡ እንዲሁም ተቀባይነት ያለው ተጨባጭ ማስረጃ ሳይኖረው ከ3ኛ ወገን የተገኙ የግብይት መረጃዎችንና የኦዲት ውጤቶችን ሊያይ አይገባውም፡፡

9. የግብር ይግባኝ ጉባዔው በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችንና ሕግን መሰረት በማድረግ ለቅሬታ መነሻ በሆነው የቀን ገቢ ጥናት ላይ ዝርዝር ማስተካከያ እስከምክንያቱ ይሰጣል፡፡

10. ስለ አበል አከፋፈል

1. በየደረጃው የሚገኘው የጉባዔ ሰብሳቢና ሌሎች አባሎች በጉባዔው ላይ እየተገኙ ለሰሩብት ጊዜ አበል ይከፈላቸዋል፡፡

2. ገቢ ጽ/ቤቱ የሚገኝበት የከተማ አስተዳደሩ ገንዘብናአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠርት ለሚያስፈልግ ወጪ የሚሆን በጀት ገቢ ጽ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች አቅደው ሲያቀርቡ በየበጀት ዓመቱ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

3. በወረዳ አስተዳድር ደረጃ ለሚቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለአበል ክፍያ የሚሆን ገንዘብ ከወረዳ ገቢ ጽ/ቤት፣ ከመሪና ንዑስ ማ/ቤት ከተሞች በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ገቢ በማድረግ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

ሀ. በከተማ/ወረዳ አስተዳደሩ የሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አባላት በጉባዔው ላይ እየተገኙ ስለሰሩባቸው ፋይሎች ብዛትና ስላስተላለፉአቸው ውሳኔዎች በገቢ ጽ/ቤቱ ኃላፊ እንዲረጋገጥ በማድረግ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ቅጽ 02 መሠረት በሰብሳቢው አማካኝነት ሪፖርት ሲቀርብላቸው አበል ይከፍላሉ፡፡

ለ. ለግብር ይግባኝ ጉባዔ አባላት የሚከፈለው አበል በሚከተለው ልክ ይሆናል፡፡

- ለጉባዔው ሰብሳቢዎች በመደበኛ ጊዜያቸው ተሰብስበው የግብር ይግባኝ ጉዳዮች አቤቱታ ባዩበት ቀን ብር 45
- የጉባዔውን ፀሐፊ ጨምሮ ሌሎች የጉባዔው አባላት በቀን ብር 35 ይሆናል፡፡

**11. የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤውን ውሳኔ ስለማሳዎቅ፡-**

11.1 የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔው በዕለቱ የታዩና ውሳኔ የተሰጠባቸውን የይግባኝ አቤቱታዎች ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ቀጥሎ ባሉት ሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት ለገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ቅጽ 01 መሰረት ሞልቶ ያስታውቃል፡፡

11.2 በዕለቱ ውሳኔ የተሰጠባቸውን የግብር አቤቱታዎች ለገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ሲያስታውቅ በግልባጭ ለከተማ /ወረዳ አስተዳደሩ የግብር ስትሪንግ ኮሚቴ ያሳውቃል፣

11.3 የግብር ይግባኝ ጉባኤው አቤቱታውን ሲመረምር የተወሰዱ አንቀጾች የሚገኙበትን ህግ የሚያብራሩና ሌሎች በዝርዝር መገለጽ አለባቸው የሚሏቸውን ሀሳቦች ሲኖሩ ከቅጹ ጋር አባሪ አድርጎ ማሳዎቅ አለበት፣

12. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

ይህ ማሻሻያ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ቀርበው በእንጥልጥል ላይ የሚገኙ የግብር ይግባኝ ጉዳዮች ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በነበረው አሰራር አፋጣኝ እልባት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

13. **ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ድንጋጌዎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

14. **መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1/2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**

**ገቢዎች ባለስልጣን**

**<u>ባህር ዳር</u>**

**ቅጽ 2**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ___________ ከተማ /ወረዳ/ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት**

የ ----------------------------------- ዞን ------------------------------- ከተማ/ወረዳ/ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉብዔ አባላት ሪፖርት ማቅረቢያና አበል መጠየቂያ ቅጽ

የ -------------------------------------------- ወር ----------------------------------- ዓ.ም.

በመቀነስ የተወሰነ ---------------------------------------

በማፅናት የተወሰነ ---------------------------------------

ውሳኔው የተሰረዘ ---------------------------------------

ድምር ---------------------------------------------

| ተ.ቁ | የጉባዔ አባሉ ሙሉ ስም | የተወከለበት መ/ቤት | በስብሰባ ላይ የተገኘበት ቀን ብዛት(ሀ) | የቀን አበል ብር መጠን (ለ) | ጠቅላላ ተከፋይ (ሀxለ) | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

**የጉባዔ ሰብሳቢ ስም ----------------------------------- ፊርማ ----------------- ቀን -------------------**